# 10 ዋናው የጥገኝነት ቃለ ምልልስ

## ለ"ትልቁ ቃለ መጠይቅ" እንዴት መዘጋጀት አለብዎ

ዩኬ

**ትልቁ ቃለ መጠይቅ ምንድን ነው?**

በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ እንዲቆዩ ይፈቀድልዎ እንደሆነ እና ጥገኝነት ይሰጥዎት እንደሆነ ከመወሰኑ በፊት ሆም ኦፊስ ብዙ ጊዜ ቃለ መጠይቅ ያደርጋል። በቃለ መጠይቁ ወቅት፣ ጥገኝነት ለመጠየቅዎ ምክንያቶች እና ለምን ወደ ትውልድ ሀገርዎ መመለስ እንደማይችሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁዎታል። ቃለ-መጠይቁ ለጥገኝነት ሂደትዎ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ክፍሎች አንዱ ነው፣ እና ስለዚህ ለቃለ መጠይቅዎ መዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው።

### ቃለ መጠይቁ መቼ እንደሆነ እንዴት ማወቅ እችላለው?

ሆም ኦፊስ ስለ ቃለ መጠይቅዎ ቦታ፣ ሰዓት እና ቀን መረጃ ይልክልዎታል። ደብዳቤ፣ ኢሜል ወይም የኤስኤምኤስ መልእክት ይደርስዎታል። ከቃለ መጠይቅዎ ከ7-14 ቀናት በፊት ይነግሩዎታል። አብዛኛዎቹ ቃለመጠይቆች የሚከናወኑት በቃለ መጠይቅ ማእከል ነው፣ አብዛኛውን ጊዜ በቪዲዮ። ለምርመራዎ ቃለ መጠይቅ አስተርጓሚ ከነበረዎት በተመሳሳይ ቋንቋ አስተርጓሚ ይሰጥዎታል።

### በቃለ መጠይቁ ላይ መገኘት ካልቻልኩኝ?

በቃለ መጠይቁ ላይ መገኘት ካልቻሉ በተቻለ ፍጥነት ለሆም ኦፊስ መንገር አለቦት። መሳተፍ ላለመቻልዎ በቂ ምክንያት ማቅረብ አለብዎት። ከታመሙ፣ ለዚህ ማስረጃ እንዲልኩ ይጠየቃሉ፣ ለምሳሌ ከሐኪም የተላከ ደብዳቤ።

ካልተገኙ እና በቂ ምክንያት ካልሰጡ፣ የጥገኝነት ማመልከቻዎ እንደ ተሰረዘ ይቆጠራል እና እርስዎም ሸሽቶ እንደመጣ ሰው ይቆጠራሉ።

### የቃለ መጠይቅ ግብዣ ደብዳቤ እንደደረሰኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

የቃለ መጠይቅ ግብዣ እንደደረሰዎት፣ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት:

- ወደ ቃለ መጠይቁ እንዴት እንደሚጓዙ ያረጋግጡ። የጥገኝነት ድጋፍ ከተቀበሉ፣ ሆም ኦፊስfice ለጉዞዎ ወጪ ይከፍላል። በሌላ ቋንቋ አስተርጓሚ ከፈለጉ፣ ይህንን ለመጠየቅ ወደ ሆም ኦፊስ ኢሜይል ይላኩ።
- ለእርስዎ አስፈላጊ ከሆነ ወንድ ወይም ሴት አስተርጓሚ እንዲኖርዎ መጠየቅ ይችላሉ።
- ቃለ መጠይቅዎ በድምጽ እንዲቀዳ ይጠይቁ።
- ለጉዳይዎ ድጋፍ የሚሆኑ ሰነዶችን ያሰባስቡ። ሰነዶቹን ከቃለ መጠይቅዎ በፊት ወይም በኋላ በኢሜል ወደ ሆም ኦፊስ መላክ ይችላሉ።

### ለቃለ መጠይቁ እንዴት መዘጋጀት አለብኝ?

ለምን ጥገኝነት እንደጥየቁ ለሆም ኦፊስ ለማስረዳት ቃለ መጠይቁ ዋነኛ እድልዎ ነው። ከቃለ መጠይቅህ በፊት፣ የታሪክዎን ጠቃሚ ክፍሎች እንዴት እንደሚያብራሩ ማሰብ አለብዎ፤ እነዚህም፡

- ለምን ከሀገር ወጡ? እንዲሰደዱ ያደረገዎ የተለየ ክስተት ነበር? ከማን ጋር ነው አደጋ ላይ ያሉት እና ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው?
- በፖለቲካ፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ፣ በብሔር ወይም በሌላ ምክንያት ነው?
- ቤተሰብዎም ከእርስዎ ጋር ተጎድተዋል ወይ?
- ወደ እንግሊዝ እንዴት እንደተጓዙ?
- ይህን ጉዞ ያዘጋጀው ማን ነው ? የከፈለውስ?
- በትውልድ ሀገርዎ ወይም ወደ እንግሊዝ በሚያደርጉት ጉዞ ላይ ድብደባ/ስቃይ ደርሶብዎታል ወይም ስራ እንዲሰሩ ተገድደዋል?
- በእነዚህ ክስተቶች ምክንያት ምንም አይነት የጤና ችግር አጋጥምዎታል?
- በእርስዎ የይገባኛል ጥያቄ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ቦታዎችን እና የሰው ስሞችን እንዲሁም የአስፈላጊ ክስተቶችን ቀናት ለማስታወስ መሞከር አለብዎት።ቀኑን ማስታወስ ካልቻሉ አንድ ነገር ሲከሰት የነበረ ሌላ መረጃ ማስታወስ ይችሉ ይሆናል፤ ለምሳሌ አየሩ በክረምት ምክንያት ቅዝቃዛ ከነበረ፣ ወይም በሃይማኖታዊ በዓላት ወቅት እየተጓዙ ከነበር።

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ በመጻፍ ወይም ጮክ ብለው በመናገር ለቃለ መጠይቁ መዘጋጀት ይችላሉ።

### ምን ይዤ መሄድ አለብኝ?

ማንነትዎን የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ይዘው መምጣት አለብዎት። ይህ የ ARC ካርድዎን፣ ፓስፖርትዎን ወይም የልደት ምስክር ወረቀትዎን፣ እና ከሆም ኦፊስ የተቀበሉትን የቃለ መጠይቅ ግብዣ ደብዳቤ ያካትታል። ቃለ መጠይቁ በአካል ካልተደረገ በስተቀር፣ ለቃለ መጠይቁ ጠያቂ ምንም አይነት ሰነድ መስጠት አይችሉም። እነዚህን ሰነዶች በኢሜል ወይም በፖስታ ወደ ሆም ኦፊስ መላክ እንዲችሉ ታሪክዎ እውነት መሆኑን የሚያሳዩ ማንኛውንም ሰነዶች መሰብሰብ አለቦት።ለምሳሌ፣ ወደ እርስዎ የተላኩ ፎቶግራፎች ወይም የጋዜጣ መጣጥፎች ወይም የማስፈራሪያ ደብዳቤ ወይም መልዕክቶች ሊኖሩዎት ይችላሉ።

# 10 ዋናው የጥገኝነት ቃለ ምልልስ

## ለ"ትልቁ ቃለ መጠይቅ" እንዴት መዘጋጀት አለብዎ

ዩኬ

**ለቃለ መጠይቁ ከእኔ ጋር ማን መምጣት ይችላል?**

የአእምሮ ጤና ወይም የአካል ድጋፍ ፍላጎት ከሌለብዎ በስተቀር ወደ ጥገኝነት ቃለ መጠይቁ ጓደኛዎን እንዲያመጡ አይፈቀድልዎትም፣ ነገር ግን ጠበቃ ማምጣት ይችላሉ። በክፍሉ ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች ጠያቂው ወይም ጠያቂዎቹ እና አስተርጓሚ እንዲቀርብ ከጠየቁ አስተርጓሚው ይኖራል።

**በቃለ መጠይቁ ወቅት ምን ሊፈጠር ይችላል?**

ጠያቂው ለምን ጥገኝነት እንደሚጠይቁ ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል። ስለ ቤተሰብዎ እና ስላለፈው ህይወትዎ ሊጠይቁዎት ይችላሉ። እንዲሁም ስለትውልድ ሀገርዎ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ አቀማመጥ፣ ፖለቲካ እና ባህል ጥያቄዎችን ይጠይቁዎታል።

**ጥያቄዎቹን እንዴት መመለስ አለብኝ?**

ስለ ህይወትዎ እና ስለ ጉዞዎ ግልጽ እና ዝርዝር መግለጫ ለመስጠት መሞከር አለብዎት። የሚጠየቁትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ ማዳመጥ አለብዎ። ጥያቄውን ካልተረዱት ለቃለ መጠይቅ አድራጊው መመንገር እንዲሁን እንዲደገም ወይም እንዲቀልል መጠየቅ ይችላሉ።

አንዳንድ ጥያቄዎች ተደጋጋሚ ወይም አላስፈላጊ ሊመስሉ ይችላሉ። የጥያቄውን መልስ የማያውቁት ከሆነ እንደማያውቁ መናገር አለብዎ።

ረጅም መልስ መስጠት አይጠበቅብዎትም። አንዳንድ ጊዜ 'አዎ' ወይም 'አይደለም' የተሻሉ መልሶች ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ቃለ-መጠይቅ አአድራጊው ስለእርስዎ ወይም ስለትውልድ ሀገርዎ ምንም እንዲያውቅ አይጠብቁ።

ሃለእርስዎ ቀላል የሚመስሉ ነገሮችን ለማብራራት ዝግጁ መሆን አለብዎት።እውነቱን መናገር እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ምክንያቱም ሆም ኦፊስ ስለ ታሪክዎ ትንሽ እንኳን እንደዋሹ ካወቀ አጠቃላይ የይገባኛል ጥያቄዎን ሊሰርዘው ይችላል።

በቃለ መጠይቁ ወቅት፣ የHome Office ቃለ-መጠይቅ አድራጊው የሚናገሩትን ሊጠራጠር ወይም ታሪክዎን ላያምን ይችላል። ይህ ሊያናድድ ይችላል፣ ስለዚህ ለዚህ ዝግጁ መሆን አለብዎ እናም ለመረጋጋት ይሞክሩ።

ቃለ-መጠይቅ አድራጊው የሆነ ነገር አምልጦታል ብብለው ካሰቡ፣ ካልተረዳዎት ወይም የሆነ ነገር ለማብራራት ጊዜ ካልሰጠዎት ይህን ለጠያቂዎ መንገር አለብዎት። በቃለ መጠይቁ መጨረሻ ላይ መጨመር የሚፈልጉት ነገር እንዳለ ሲጠይቁ ይህን ማድረግ ይችላሉ።

**እረፍት ማድረግ ካለብኝስ?**

በቃለ መጠይቁ ወቅት እረፍት መውሰድ ይችላሉ። ይህ ምናልባት ስለደከመዎት ወይም አንድ ጥያቄ ስላናደድዎ ወይም ጥሩ ስሜት ስለማይሰማዎት ሊሆን ይችላል። ቃለ-መጠይቅ አድራጊው ብዙውን ጊዜ እረፍት ይሰጥዎታል ነገር ግን ቀድመው እረፍት መጠይቅ ይችላሉ።

**ካልገባኝስ?**

አንድ ጥያቄ ካልገባዎት፣ ጠያቂው እንዲደግመው መንገር አለብዎ። አስተርጓሚውን ካልተረዱትም **አዲስ አስተርጓሚ እንዲዘጋጅ በተቻለ ፍጥነት ለቃለ-መጠይቅ አድራጊው መንገር አለብዎ።**

**ከቃለ መጠይቁ በኋላ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ከቃለ መጠይቁ በኋላ፣ የቃለ መጠይቁን የጽሁፍ ግልባጭ ወደ እርስዎ እንዲላክ በድጋሚ መጠየቅ አለብዎት። ይህ በቃለ መጠይቁ ወቅት የተጠየቁትን በሙሉ የያዘ ነው።

የድምጽ ቅጂም እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይችላሉ። ግልባጩን ለማንበብ መሞከር እና ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ይሞክሩ።ስህተት ካለ፣ በተቻለ ፍጥነት ለሆም ኦፊስ መንገር አለቦት። ሆም ኦፊስ አንዳንድ ሰነዶችን እንዲሰጡ ከጠየቅዎ ወይም ታሪክዎን የሚያረጋግጡ ሌሎች ሰነዶች/ማስረጃዎች እንዳሉ ካስታወሱ በተቻለ ፍጥነት ወደ ሆም ኦፊስ መላክ አለብዎ። ብዙውን ጊዜ ይህንን በ 5 ቀናት ውስጥ መፈጸም አለብዎት።

ከቃለ መጠይቁ በኋላ ለመዝናናት ጊዜ ለመውሰድ ይሞክሩ። በጣም አስደናቂ ተሞክሮ ሊሆን ይችላል።

**አንድ ጠቃሚ ነገር ከረሳሁስ?**

አንድ ጠቃሚ ነገር ከረሱ፣ በተቻለ ፍጥነት ለሆም ኦፊስ መንገር አለቦት። በተቻለ መጠን ስለሁኔታዎ በዝርዝር መናገር አለብዎ እናም የተናገሩትን ነገር የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ማሳየት አለብዎት።